# 2. ሐኪም መታየት

## የስፔሻሊስት ሐኪሞች

- የበለጠ ምርመራ ወይም ሕክምና የሚያስፈልግዎት ከሆነ፡ የቤተሰብ ሐኪምዎ፡ ወደ ስፔሻሊስት ሊልክዎት ይችላል። ስፔሻሊስት የሚባሉ በአንድ የተለየ የጤንነት ችግር ላይ ያጠኑ ሐኪሞች ናቸው።
- በስፔሻሊስት ለመታየት በሚሄዱበት ጊዜ፡ ብዙ ጊዜ ከቤተሰብ ጠቅላላ ሐኪምዎ፡ እንደተላኩ የሚያሳይ ደብዳበ ያስፈልግዎታል። በስፔሻሊስቱም በቀጥታ መታየት ይችላሉ። ነገር ግን በቤተሰብ ጠቅላላ ሐኪም ያልተላኩ ከሆነ ከመዲኬር የሚያገኙትን ተመላሽ ገንዘብ ይቀንሳል።
- የስፔሻልስት ሐኪሞች ከቤተሰብ ጠቅላላ ሐኪሞች ይወደዳሉ። አብዛኖቹ ስፔሻሊስቶች የbulk bill አገልግሎት አይሰጡም። ስንት እንደሚያስከፍሉ አስቀድሞ ማወቅ ጠቃሚ ነው።
- የቤተሰብ ሐኪምዎ በህዝብ ሆስፒታል ወደሚሰራ ስፔሻሊስት ሊልክዎት ይችላል። ቀጠሮ ለመያዝ ትንሽ ይጠብቁ ይሆናል። በየህዝብ ሆስፒታል በሚሰሩ ስፔሻሊስቶች እየተመላለሱ ለመታከም ከፈለጉ በነጻ መታከም ይችላሉ። ስፔሻሊስት ሐኪሞች፡ በግል ክሊኒኮች ውስጥም ይሰራሉ።

## መድሀኒቶች

- የቤተሰብ ሐኪምዎ እና/ወይም ስፔሻሊስቱ የሐኪም ትእዛዝ ጽሑፍ ለመድሀኒት ሊሰጥዎ ይችላል። ይህን ጽሑፍ ይዘው ወደ ኬሚስት/ፋርማሲ ይሄዳሉ
- የመዲኬር ካርድ፣ የጤና እንክብካቤ ካርድ፣ ወይም የጥሮታ አበል (Pension Concession) ካርድ ካልዎት ይዘውት ወደ ኬሚስቱ/ፋርማሲ ይሂዱ። እነዚህን ካርዶች ለማግኘት እንዴት እንደሚችሉ የበለጠ መረጃ ማግኘት ከፈለጉ ወደ Centrelink Multilingual በስልክ ቁጥር 131 202 ደውለው ይጠይቁ
- መድሀኒቱን በሚገዙበት ጊዜ እንዲከፍሉ ይጠየቃሉ፡ ነገር ግን እነዚህን ካልዶች ለያዙ ሰዎች አብዛኞቹ መድሀኒቶች በቅናሽ ዋጋ ይሸጣሉ
- የበለጠ መረጃ ለማግኘት መረጃ ጽሑፍ 3 - መድሀኒቶች የሚለውን ይመለከቱ

| ስፔሻሊስት ሐኪም | በሙሉ አተኩራቸው |
|---|---|
| አለርጊስት/ኢሚኖሎጂስት | ለምሳሌ አለርጂና አስም |
| ካርዲኦሎጂስት | ልብ |
| ደርማቶሎጂስት | የቆዳ በሽታ |
| ኢንዶክሪኖሊጂስት | የእጢና የሆርሞን ለምሳሌ የስኳር በሽታ |
| ጋስትሮኢንትሮሎጂስት | የጨጋራ፣ አንጀት፣ምግብ መዋሀድ |
| ጀሪኣትሪሻን | ሽማግሌ ሰዎች |
| ጋይኖኮሎጂስት | የሴት የአባለ ዘር |
| ሀማቶሎጂስት | ደም |
| ሄፓቶሎጂስት | ጉበት |
| የተላላፊ በሽታዎች ሐኪም | ተላላፊ በሽታ ለምሳሌ፡ ኩፍኝ፣ HIV |
| የኦንኮሎጂስት ሐኪም | የካንሰር ሕክምና |
| ኔፍሮሎጂስት | ኩላሊት |
| ኒሮሎጂስት | አንጎል |
| ኦብስቲሪሺያን | ልጅ መውለድ |
| ኦኩፔሽናል ሐኪም | ቁስል/ሕመም |
| ኦፍታልሞሎጂስት | የአይን ማየት |
| ኦርቶፓዲስት | አጥንት፣ ጡንቻ፣ መገጣጠምያ |
| የኦቶላርይኖሎጊስት/ENT | ጆሮ፣ አፍንጫ፣ እና ጉሮሮ |
| ፐዲያትሪሻን | ልጆች |
| ፓቶሎጊስት | በሽታን/ሕመም ለይቶ ለማወቅ ሴሎችና የሰውነት ቲሹን መመርመር |
| ፋርማኮሎጊስት | የመድሀኒት/ክኒን ውጤት በሰውነት ላይ |
| የፓሊያቲብ መድሀኒት ሐኪም | በበሽታ እና በሞት ጊዜ የመስቃየት ጊዜ |
| ሳኪያትሪስት | የአእምሮ በሽታ |
| ራዲኦሎጂስት | በሰውነት ውስጥ ምስል ማየትና ትርጉሙ ማወቅ (ለምሳሌ፡ ራጂ) |
| ኒማቶሎጂስት | ጡንቻና የካላል ቅርጽ ለምሳሌ፡አርትሪትስ |
| የቀዶ ጥገና ሐኪም | ቀዶ ጥገና |
| የቶራሲክ መድሀኒት | የደረት፣ ትንፋስ |
| ኡሮሎጂስት | የሽንት መቆጣጠር፡ኩላሊት፣ ዩረተር፣ፊኛ እና ዩረትራ ያጠቃለለ |

© QUEENSLAND HEALTH - JUNE 2007